«በዓላማ ፅናት በቁርጠኝነት ለሚመጡ በራችን ክፍት ነው»

የቀድሞው የትንጅት ፕሬዚዳንት ኢ/ር ኃይሉ ሻወል ባለፉት 9 ወራቶች በሰሜን አሜሪካ በህክምናና በፓርቲው ሥራ ላይ ከቆዩ በኋላ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ፡፡

የኢንጅነር ኃይሉ ሻወል ጤና ተሟልቶ ወደ አገራቸው መመለሳቸውን ምክንያት በማድረግ በየደረጃው የሚገኙ የትንጅት ሰአንጅነትና ለደሞክራሲ ፓርቲ አመራሮች አባላትና ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች በተገኙበት ቸርችል ጎዳና በሚገኘው የቀድሞው ትንጅት ጽ/ቤት ደማቅ አቀባበልና የራሊፕሽን ግብዣ ተደርጎላቸዋል፡፡

ኢንጅነር ኃይሉ በትንጅት ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ በተገኘለሰ ድንኳን ውስጥ አቀባበል ሲደረግላቸው «ጤንነቴ ተሟልቶ በምወጣት አገሬና ከማፈቅራቸው የትግል ጓደኞቼ መካከል በመገኘቴ በደስታ ተወጣለሁ፤ ለዚህ ያበቃኝንም አምላኬን አመሰግናለሁ» ብለዋል፡፡ በተጨማሪም «ፓርቲያችን በዓላማ ፅናት በአውነትና በቁርጠኝነት ለሚመጡ ሁሉ በራችን ክፍት ነው፤ ነገር ግን ለሌላ አካል መልዕክተኛ ሆኖ መምጣት ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ አገራችንን ለመገንባት ሕዝቡ ተፋቅሮ፣ ተከባብሮ፣ በአኮልነትና በአንድነት እንዲኖር ለማድረግ ሁላችንም የጋራ ኃላፊነት አለብን፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ከአኛ ጋር ሲታገል ኖሮአል፤ የፓርቲ አባላት ያልሆኑ ወገኖቻችን እንኳን ለሕዝብ ዓላማሲሉ ተሰውተዋል» ብለዋል፡፡

ኢ/ር ኃይሉ ከሚመሩት የቀድሞው ትንጅት ፓርቲ የወጣው ፕሮግራም እንደሚያስረዳው ኢ/ር ኃይሉ ሻውል በዚሁ ሣምንት ለአገር ውስጥና ለዓለም ጋዜጠኞች ጋዜጣዊ መግለጫ እንደሚሰጠና በቀጣይ ጥቂት ቀናት ውስጥም ከትንጅት ሳዕላይ ምክር ቤት አባላት ጋር ሰፊ ውይይትና ምክክር ካደረጉ በኋላ የፓርቲያቸውን ጠቅላላ ጉባኤ እንደሚጠሩ ታውቋል፡፡

በአቀባበሉ ሥነ ስርዓት ላይ የአዲስ አበባ ሴቶች ተወካይ ወ/ሮ አሳግስሁ ሞገድ፣ የአደስ አበባ ወጣቶች ተወካይ ወጣት ጌታህ ዓለም፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተወካይ ሻለቃ እርጋው ኩቢታሙ፣ የፓርላማ የትንጅት አባላት ተወካይ የተከበሩ ሽዋፈራ ይጥና፣ የምስራቅ ሽዋ ዞን የትንጅት ተጠሪ አቶ ነቢዩ ክንፈ፣ የአዲስ አበባ የአስሩ ክፍለ ከተሞች ተወካይ እና የሰኔ 1/97 ሰማዕታት ቤተሰቦች ተወካይ ንግግር አድርገዋል፡፡

እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተወካይ፣ የሴቶች ኮሚቴና የወጣቶች ኮሚቴ ተወካይና በስዊድን የትንጅት ድጋፍ ሰጭ ተወካይ ለኢ/ር ኃይሉ ሻወል የአበባ ስጦታ አበርክተዋል፡፡ የትንጅትን ጉዳይ በተመለከተ ያቀናበርነውን ሰፊ ዘገባ እንደሚከተለው አቅርበናል፡-

የቀድሞው የትንጅት አመራሮች ሐምሌ 13 ቀን 1999 ዓ.ም ከአስር ከተፈቱ በኋላ ፓርቲው እንደገና ያንቀሳቀል የሚል አምነት በህዝብ ዘንድ አሳድሮ ነበር፡፡ ነገር ግን ከአስር የተፈቱት አመራሮች በድን ሆነው ወደተለያዩ ክፍል አሳማት ከተገባው በኋላ ያልተጠበቀ ክስተት ተፈጠረ፡፡

በወቅቱ ወደ አሜሪካ እንዲገቡ የተወሰኑት ስድስት የልዑካን ቡድን አባላት እንደሆኑ የተገለፀ ቢሆንም፣ ኢ/ር ኃይሉ ሻወል ከቡድኑ ጋር ሳይገባ መቅረታቸው ተነግሮ ነበር፡፡ ለዚህም ከተገገሮች አምስት የልዑካን ቡድን አባላት እንደምክንያት የተረበው ሺዛ አለማገኘታቸው ነበር፡፡

ሆኖም ኢ/ር ኃይሉ ሻወል ከሦስት ሳምንት በኋላ ለክፍተኛ ህክምና በአውሮፓ በኩል አድርገው አሜሪካ እንደገቡ፣ ከልዑካን ቡድኑ ጋር ልዩነት እንዳላቸው በይፋ ታውቀ፡፡

ኢ/ር ኃይሉ ሻወል በወቅቱ ለጋዜጠኞች በሰጡት አስተያየት እንደገለፁት ከሦስ፣ ከአስር እንደተፈቱ ወገር ቤት ያለውን ህዝብ ማደራጀት፣ የተዘጉ ቢሮዎችን መክፈት፣ የተጎዱ ቤተሰቦችን ማፅናናት ሲገባ ወደ አሜሪካ ለመጓዝ መቸኮል አግባብ አልነበረም የሚል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች የልዩነት ነጥቦችን መጥቀሣቸው ይታወሳል፡፡

የአሜሪካኑን የልዑካን ቡድን ይመሩ የነበሩት ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሣ የኢ/ር ኃይሉ ሻወል የልዩነት ነጥብ ትክክል አለመሆኑን፣ እሣቸው የዘገዩት በጤና እክልና በቪዛ መዘግየት መሆኑን ጠቁመው፣ አብረዋቸው የአሜሪካኑን ተልዕኮ እንዲወጡና እንዲመሯቸው ተማፅኖ አስከማቅረብ ደርሰው ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ሁለቱም ወገኖች ልዩነታቸው እየሠፋ ሄደ፡፡ እነ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሣ በአሜሪካ የተለያዩ ስቴቶች ቅስቀሣ ሲያካሂዱ፣ ኢ/ር ኃይሉ ሻወል በበኩላቸው ከአስር ከተፈቱ ሌሎች ጥቂት የቀድሞው የትንጅት አባላት ጋር (ከአቶ በድሩ አደምና ንግስት ገ/ህይወት ጋር በመሆን) በፊናቸው መቀስቀስ ቀጠሉ፡፡ ይሄኔ ነው ከአስር ከተፈቱት ሁለቱ የትንጅት አመራሮች መሃል የማይታረቅ ቅራኔ እንደተፈጠረ እርግጥ የሆነው፡፡

በሁለቱ ወገኖች መሀል ልዩነት መፈጠሩን የሰማው ህዝብ የደነገጠና ያዘነ ቢሆንም፣ አመራሮቹ ወደ አገር ቤት እንደተመለሱ ሁኔታዎች ይለወጣሉ፣ እንደገና አንድ ይሆናሉ የሚሉ ተስፋ አሳድሮ ነበር፡፡

ይህ በአንዲህ እንዳለ በወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሣ የሚመራው የልዑካን ቡድን ተልዕኮውን አጠናቆ ወደ አገር ቤት መመለስ ጀመረ፡፡ የልዑካን ቡድኑ ሞተር እንደነበሩ የሚነገርላቸው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ግን ወደ አገር ቤት ሳይመለሱ ቀሩ፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ለ6 ወር ያህል እዛው አሜሪካ እንደሚቆዩ ተገለፀ፡፡ የዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ለ6 ወር ባህር ማዶ መቆየት የፓርቲውን እንደገና ተጠናክሮ መቆም ተስፋ ያርቃል፣ ትግሉን ያዳክማል የሚል ስሜት አሣደረ፡፡

ኢ/ር ኃይሉ በበኩላቸው ሕክምናቸውን እስከሚያጠናቅቁ እዚያው እንደሚቆዩ ገለፁ፡፡ የሁለቱ ወገኖች ባህር ማዶ መቆየት ለችግሩ መፍትሔ የሚሰጥበትን ጊዜ ያርቃል የሚሉ ወገኖች በረከቱ፡፡ የልዩነቱ ዋነኛ ምክንያቶች ተደርገው የተቆጠሩት ኢ/ር ኃይሉ ሻወልና ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እንደሆኑ በሰፊው ይነገር ጀመር፡፡

በዚህ መሀል በታህሳስ ወር 2000 ዓ.ም ኢ/ር ኃይሉ ሻወል ጠቅላላ ጉባኤ ተካሄዶ ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሣ፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አቶ ብሩክ ከበደ፣ ኢ/ር ኃይሉ አርአያ እና ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራሁ በትንጅት ስም እንዳይንቀሣቀሱ የሚያዝ መግለጫ አወጡ፡፡ አከታትለውም ሀገር ውስጥ ያለውን ትንጅት በተጠባበቂ ሊቀመንበርነት እንዲመሩ አቶ አባይነህ ብርሃኑን መወከላቸውን አሳወቁ፡፡ በሁለቱ መከፋል የተፈጠረው ልዩነት ጥራሹን የለየለት ከዚህ በኋላ ነው፡፡

ከቀድሞው የትንጅት ሳዕላይ ም/ቤት አባላት 20 የሚሆኑት ከነ ወ/ሪት ብርቱካን ጎን ተሰለፉ፡፡ ፓርላማ ከገቡት የትንጅት ተመራጮች ጋር በመደራደር አዲስ ፓርቲ የመመስረት እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡

አዲሱን ፓርቲ ለመመስረት የፌርማ ማሰባሰብ በሚደረግበት ወቅት ከቀድሞዎቹ 20 የላዕላይ ምክር ቤት አባላት መካከል ሁለቱ፣ (አቶ ሙሉነህ ኢዶኤልና ዶ/ር በፈቃዱ ደግፌ) ከእነ ብርቱካን ወገን ጋር መሰባሰባቸውን አቆሙ፡፡ ይሁን እንጂ ምክንያታቸውን በይፋ አልገለፁም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በሀገሪ አሜሪካ የሚገኙት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና ሌሎች አራት የቀድሞው ትንጅት ላዕላይ ም/ቤት አባላት አሁን ባለው ሁኔታ በኢትዮጵያ ሠላማዊ ትግል ማካሄድ እንደማይቻል እና ሌላ የትግል ስልት መቀየስ እንደሚገባ በተለያየ መንገድ (በንግግርና በፅሁፍ) መግለፅ ጀመሩ፡፡ ይህ ሁኔታ በህዝብ ዘንድ እነ ብርሃኑ ነጋ ወደ ትጥቅ ትግል ሊገቡ ነው እንዴ የሚል ጥያቄ አስነሣ፡፡ የእነ ዶ/ር ብርሃኑ ሌላ አማራጭ የመከተል አዝማሚያ ሀገር ውስጥ በመንቀሣቀስ ላይ ባለው ወገን ተቀባይነት እንደሌለው በመግለፅ በወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሣ ፊርማ መግለጫ ወጣ፡፡ የሶስቱ ወገን አሠላለፍ፣ አነጋጋሪም አደናጋሪም እየሆነ ሄደ፡፡

የሆነ ሆኖ አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ የተሰኘ አዲስ ፓርቲ ለማቋቋም ፊርማ ማሰባሰቡን የገለፀው የእነ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሣ ቡድን ፕሮግራሙንና ሌሎች ሰነዶችን የማዘጋጀት ተግባሩን እጠናቆ ፓርቲውን በይፋ ለመመስረት የሚያስችል ጠቅላላ ጉባኤ ሰኔ 7 ቀን 2000 ዓ.ም እንደጠራ በይፋ አሣወቀ፡፡

ከሣምንት በፊት ሀገር ውስጥ ከሚገኘው ከቀድሞው የትንጅት ፓርቲ ማንኛውም ቡድን ጋር በይፋ መለየታቸውን የገለፁት እና በሀገር አሜሪካ የሚገኙት እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም «ግንቦት 7 ንቅናቄ» የተሰኘ ፓርቲ መመስረታቸውን በይፋ አሳወቁ፡፡ በዚህ ቀን እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የትግል ስልታቸው ሁሉንም የትግል ስልት ያካተተ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

አይደለም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ መስዋዕትነት የከፈለበት ስለሆነ መልሶ ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ ሠላማዊ ትግል ውጤት የሚያስገኘው በፓርቲዎች ጥንካሬ እንጂ እንዲሁ ያዝ ለቀቅ በሚደረግ አሠራር አይደለም» ብለዋል፡፡

ኢ/ር ኃይሉ ሻወል ያገዷቸውን ሰዎች በተመለከተ «የአምስቱ ሰዎች እገዳ ጉዳይ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰን እንጂ በኃይሉ ሻወል የሚወሰን አይደለም፣ ጠቅላላ ጉባኤው ይቀጥሉ ካለ ይቀጥላሉ፣ ካገዳቸው ይታገዳሉ» ብለዋል፡፡

ከሠላማዊ ትግል ስልት ውጪ ሌላ

ከቀድሞው የትንጅት ሊቀመንበር ጥቂቶች ሰኔ ሰባት ቀን አዲሱን ፓርቲ በይፋ ለመመስረት ጠቅላላ ጉባኤ በጠሩበት እና እነ ዶ/ር ብርሃኑ ግንቦት 7 የተሰኘ እንቅስቃሴ መደመራቸውን ባሳወቁ ማግስት፣ ሳይታሰብና ሳይታሰም የኢ/ር ኃይሉ ሻወል አ/አበባ መግባት አነጋጋሪ ጉዳይ ሆኗል፡፡

ኢ/ር ኃይሉ ሻወል ዕለተ ሰኞ ግንቦት 25/2000 በቀድሞው መኢአድ /ትንጅት ቢሮ/ አቀባበል የተደረገላቸው ቢሆንም፣ በአቀባበል ስነ ስርዓቱ ላይ ጋዜጠኞች እንዲገኙ አልተፈቀደም፡፡ ሐራምቤ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ኢ/ር ኃይሉ ሻወልን ለማነጋገር ጥረት ቢያደርግም በተናጠል ለጋዜጠኛ መግለጫ አይሰጡም የሚል ምላሽ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ኢ/ር ኃይሉ ሻወል ከጀርመን ድምፅ ሬዲዮ የአዲስ አበባ ዘጋቢ ጋር አጭር ቃለ ምልልስ አድርገዋል፡፡

ኢ/ር ኃይሉ ሻወል በዚህ አጭር ቃለ ምልልስ በፓርቲው ውስጥ የተፈጠረውን መከፋፈል በውይይት ለመፍታት ብሎም ፓርቲውን ወደ ታላቅነት መልሶ ትግሉን በሠላማዊ መንገድ ለመቀጠል በቅርቡ ጠቅላላ ጉባኤ እንደሚጠሩ፣ ይህም ቀዳሚ አጀንዳቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የያኔውን ህልውና መልሶ በሕግ የማስጠበቁ ጉዳይ የዚህ ቀዳሚ አጀንዳ አንድ አካል መሆኑን አስምረውበታል፡፡

«ቅንጅትን እንዲሁ እንደዘበት የምናየው አይደለም፣ ይህ ድርጅት የኢትዮጵያ ህዝብ ድርጅት ነው፡፡ የእኔም አይደለም፣ የማንም አማራጭ እንደሌለ የጠቆሙት ኢንጅነር ኃይሉ ሻወል «ከሠላማዊ ትግል ስልት ውጪ ያለ አማራጭ የቅንጅት መርህና አማራጭ ስላልሆነ ሌላ አማራጭ የመረጡ ከድርጅቱ ጋር የመቀጠላቸው ነገር



አብቅቷል፣ እኔ የምናገረው ከአንዱ ውጪ ስለ አራቱ ነው፡፡ የአራቱ ጉዳይ ነው በጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰነው፡፡ አንዱ ራሱን አግልሏል» በማለት የዶ/ር ብርሃኑ ነጋን አስከመጨረሻው መሠናበት አፅንኦት ሰጥተውበታል፡፡

www.abbaymedia.com